# ለመሆኑ ተሳዳቢው ማነው?

ከአቶሰውየው

በቅርቡ አንድ የማከብረው ወገኔ ጠፍቶ ኖሮ ከሥራዬ ደውሎልኝ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ላለፈው 25 ዓመታት እንደምናደርገው ሁሉ ስለ ሀገራችን ጊዜያዊ የፖለቲካ ሁኔታ ማላዘን ገባን። ብዙም ሳንቆይ የደወለበትን ዋናውን ምክንያት እንድሰማው የፈለገው መልዕክት ያለ ይመስል በኢሕአፓ ውስጥ የተፈጠረውን ሁኔታ ያብራራልኝ ገባ።

ቀጥሎም ድርጅቱ በሌሎች ድርጅቶች ጣልቃ እየገባ የሚያፈርስ ነው ብሎ በማስረጃነትም የቅንጅትን መከፋፈል አንደኛውን በመወገን አባብሷል የሚለውን የጠነዛ የአንጃኛው ቡድን መሪዎች እነ ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው የሚያነበንቡትን ደግሞልኝ እንዲያውም አንዳንድ የኢሕአፓ አምራር አባላት በየድረ-ገጹ የስድብ ጽሁፍ በትነዋል ብሎ ወሬውን ይቀጥላል።

ላለፉት አራት ወራት ያልሰማሁትን ስላልነገረኝ ባይገርመኝም ፤ እንደሚከተለው ጥያቄዎች አቀረብኩለት። ስማ እንጂ ወንድም ዓለም ከጥቂት ወራት በፊት ፕሮፌሰር መስፍን በህንድ አገር ለህክምና ሄደው የቅንጅት ችግር ገና ከጅማሮው እንደነበር ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ ሰምተሃል? ኢሕአፓስ በድርጅት ጣልቃ ገብቷል ብለህ ትልቅ ክስ ስታቀርብ ፣ በልሳኑ ዴሞክራሲያ ወይም በራዲዮ ጣቢያዎቹ ቅንጅትን ወይም አመራሮቹን አስመልክቶ የሰጠው መግለጫ አለ? ካለም በምን ቀንና ቅጽ ወይም ቁጥር? አመራሮቹ የስድብ ጽሑፍ በየድረ-ገጹ ጽፈው በትነዋል ለምትለው ደግሞ ስለየትኛው ጽሁፍ ነው የምታወራው? በዚህ ጽሁፍ በዚህ መስመር የተጻፈ ብለህ የምታቀርብልኝ አለ? ብዬ ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች ቀጥተኛ መልስ መስጠት ተስኖት አራምባና ቆቦ ሲዘል ሰምቼ ፤ ሀገራችን በወሬ እየተፈታች እንዳለች አዝኜ ፤ በል እንግዲህ አሁን ሥራ ላይ ነኝና መልሼ ልደውልልህ ብዬ ተለያየን። ከዚያን ቀን በኋላ እኔም አልደወልኩለትም እሱም እንዲሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ 'የተቃዋሚ ተቃዋሚን ታጋይ ጀግኖች' በሚል ለተጻፈ የስድብ ውርጅብኝና የታሪክ ክለሳ ለሚያዥጎደጉድ ጽሁፍ ፤ የሰጠሁትን ምላሽ አስመልክቶ የተለያዩ ክሶችና በቀጥታም ሆነ በሰው ስሞታዎች ደርሰውኛል። እዚህ ላይ ለስሞተኞቹ የማሳስበው ፤ በምላሼ ያስቀመጥኩት ውሸት ካለ ቃል በቃል አውጥታችሁ ማጋለጥ ፈንታችሁ መሆኑን እያስገነዘብኩ ፤ በተለይም ደግሞ ምላሽ የሰጠህበት ጽሁፍ ባለቤት እኔ ነኝ እንጂ አንተ እንዳስቀመጥከው ዶ/ር ጌታቸው አይደለም ፤ ስሜ እገሌ ይባላል ፤ በዚያ ጽሁፍ ውስጥ ያስቀመትኩት ሙሉ በሙሉ ዕውነት ነው ፤ ብሎ መቅረብ ያባትም የናትም ሆኖ ፤ ለብዕር ስሙ እንጂ ለዶ/ር ጌታቸው መልስ መስጠትህ ውሸት ነው ብላችሁ ለምትነዘንዙኝ ምን ለማለት ፈልጋችሁ እንደሆነ ግራ አጋብቶኛል። ምናልባትም ዶ/ር ጌታቸው አይሳደብም ለማለት ይሆን? ታዲያማ ተሳዳቢው ማነው?

ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው በየመድረኩ እየወጣ የሚያዥጎደጉደውን አጸያፊ አባባል ተወት ላድርግለትና ፣ ኢሕአፓ ይውደም ብሎ ጥሎ የሄደውን ድርጅት በቅርቡ ተቀላቅሎ 'ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ' እንዲሉ በድርጅቱ ውስጥ ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ በሚስጥር የፈጠረውን አንጃ ይዞ ወጥቶ እውነተኛው ኢሕአፓ (ያውም ዴሚክራሲያዊው) እኛ ነን ሲለን ለሕዝብ ያለውን ንቀት በማያጠራጥር ሁናቴ ያስመዘገበው ማን ሆኖ? ከወያኔ ጋር አንጥፎ ሊተኛ በካናዳ ኦቶዋ በወያኔ ጋሻ ጃግሬዎች ታጅቦ 'ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ዥግራ ናት' እንዲሉ ፣ ታማኝ ተቃዋሚ ብሎን የሰደበን ማነው? የጋራ አመራር ባለበት ኢሕአፓ ውስጥ ሁለት አምባገነኖች የአመራር አባላት አላሠራ አሉን ፤ ስለሆነም ድርጅቱን እንድንከትፍለው አስገደዱን ብሎ ሳይቀፈው የብተና ሥራውን ሊሸፍን ሲያቅራራ የሚሳደበው የኢትዮጵያን ሕዝብ ፤ አብረው ይሠሩ የነበሩትን ከድርጅቱ ጋር የቀሩትን አብዛኛውን አምራርና ጓዶቹን ፤ እንዲያውም ራሱንም እየሰደበ መሆኑን ያልተረዳው ጌታቸው አይደለምን? ታዲያ ተሳዳቢው ማን ነው?

የአንጃው ጉድማ ተቆጥሮ አያልቅም። ከአንጀኞች ጋር የሄደ አንድ የማከብረው ወገኔ ገና በግርግሩ ወቅት ሁኔታውን አስመልክቶ ምነው? ምን ነካችሁ? ቅራኔውን እዚያው ድርጅቱ ውስጥ ለመፍታት አልቻላችሁምሳ? ያቀረባችሁትስ ሃሳብ በጊዜው የብዙሃኑን ጆሮ ካላገኘ ወደፊት እስከሚያገኝ ድረስ የድርጅታችሁን አንድነት ጠብቃችሁ የውስጥ ትግሉን የማትቀጥሉ ነበር? በተለይም አሁን ኃይላችንን አሰባስበን በአንድነት መቆም በሚገባን ታሪካዊ ወቅት ለምን? ብዬ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያነሳን ስንጨዋወት ፤ አዬ! ድርጅቱ አንተ የምታውቀው አይደለም! በበኩሌ እያሱና ፋሲካ ባሉበት ድርጅት ውስጥ መቀጠል አልችልም ቢለኝ ፣ በመገረም መልሼ እኽ? አንተ ከድርጅቱ ተመልሰህ የተቀላቀልከው ትላንት ፤ ከነሱ ጋር አብሬ በኮሚቴ ውስጥ ሠርቼ ይሄንና ፣ ይሄንን አምባገናናዊ ባሕርይ አይቼባቸዋለሁ ልትለኝ ካልቻልክ አሁን አንተ እያደርግህ ያለው ምን እንደሆን ታውቃለህ? ምንም በድርጅቱ ውስጥ ባልኖር የእኔን የማሰብ ችሎታ (you are insulting my intelligence) ብዬ አምርሬ ተናገርኩት። እስኪ ተሳዳቢው ማነው? እንደኔ ይህንን የተገነዘበ ቢናደድ ፣ ቢቃጠል ፤ ተስፋ ቢቆርጥ አለፍ አለፍ ብሎም ኃይለ-ቃል በተሞላ አነጋገር እምቢታውን በንዴት ፣ በስሜት ቢያስመዘግብ በማን ሊፈረድ? ወገኖቼ ሀገራችን በወሬኞች እየተፈታች ነው!!

የዘንድሮ የሀገራችን ፖለቲከኞች ሕዝቡ ያልፈለገውንና ያልጠየቀውን እየተገበሩ ተጠያቂነት ሲመጣ ተሰድብን ኡ!ኡ! ማለት የተለመደ ሆኖአል። በግሌ ብልግናን ፤ ተሳዳቢነትን አልደግፍም። የፖለቲካውም እሰጥ አገባ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የተሞላበት ቢሆን የሚጠላ የለም። ካለበቂ ማስረጃም ሆነ ምክንያት የሰው ስም በከንቱ እንዲነሳ አልፈልግም። አንዳንዴም በስሜታዊነት ብቻ በቂ ማስረጃ ሳያቀርቡ የሚረባረቡ ወገኖችን እቃወማለሁ። ነገር ግን ፖለቲከኞቻችን ሊገነዘቡት የሚገባው አንድ ነገር አለ። ይኸውም ሕዝቡ አይናቸውን አፍጠው ፤ ጥርሳቸውን አግጠው የሚዋሹትን ፤ የሕዝቡን ትግል የወያኔ ተላጣፊ ለማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፤ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ በዴሞክራሲያዊው ትግል ጋሬጥነታቸው ለሚያረጋግጡ ፖለቲከኞች ፣ ለበታኞችና ለዘረኞች እምቢኝ የማለት ሙሉ መብቱ የተጠበቀ መሆኑን ነው። ስለሆነም በእኔ ግምት እበላ ባይ ፖለቲከኞች እያዋከቡት ሕብረተ-ሰቡ በደል ሲደርስበት አይ! ይብቃ! ብሎ ኃይለ ቀል የተሞላም አነጋገር እንኳ ይዞ ቁጣውን ቢያስመዘገብ ተሳዳቢ ብሎ መፈረጅ ራሳችሁን ሳንሱር አድርጉ እኛ የፈለግነውን እናደርግ ፣ አትናገሩን ብሎ መሳደብ ነው እላለሁ። ስለዚህም ተሳዳቢዎቹ በዳዮቹ እንጂ ተበዳዩ የሕዝብ ወገን ሊሆን አይችልም። ሕብረት በምንጠይቅበት ጊዜ በውሃ ቀጠነ ድርጅት የሚሰነጥቁ ፤ ወያኔ ቁጭ ብሎ ታጋዮችንና አታጋይ ድርጅቶችና ግለ-ሰቦች ላይ የሚያረባርቡንን ፤ ኅብረ-ብሄራዊ የፖለቲካ አወቀቀር እንዳይኖርና የአንድነት ኃይሉ እንዳይፈረጥም በዘር ፣ በጎጥ ፣ በአምቻ ፣ በጋብቻ ፣ ላይ የተመሠረቱ ፖለቲካ ቡድኖች ጠባብ ማለያዎች ባንገታችን እያጠለቁልን እርስ በርሳችን እንድንተናነቅ እያደረጉ ለሀገራችን እየታገልን ፣ እያታገልናችሁ ነው የሚሉንን ሃሳዊ መሲሆች ወይግዱልን ማለትና ማጋለጥ ስድብ አይሆንም።

እኔ ለምሳሌ መላልሼ የማነሳቸው ዕውነታዎች አሉ። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በፃፈው ባለ ብዙ መቶ ገጾች ምጽሐፍ ሽፋን ላይ (በውስጡ እኔ እኔ እኔ የሚለውን ገና ቆጥሬ አልጨረስኩም) ሻእብያና ወያኔ በጠብመንጃ የቀረጹትን የኢትዮጵያ ካርታ አሳትሞ ማውጣቱ ምን የሚሉት አድርባይነት ነው ስላልኩኝ ክብረ ነክ ስድብ ተሳድበሃል ልባል እችላለሁ። ክብር በግብር የሚመጣ እንጂ ፤ ሕዝቡ ስለመረጠኝ ፣ ለብዙ ዓመታት ስለታሠርኩ ፣ ስለቆሰልኩ ስለደማሁ ወዘተርፈ እኔ ትክክል ንኝና ጉሮ ወሸባዬ በሉልኝ ብሎ የሚመጣን መሪ ነኝ ባይ ፤ አንተ ማነህ? ዛሬ ምን እየሠራህ ነው? ብሎ መጠየቅ ስድብ ሊሆን ከቶውንም አይችልም። ከተሳፈርኩብት አውቶቡስ ጠና ያሉ ሰው ኪሴን ሲያወልቁ እጅ ከፍንጅ ብይዛቸው ሌባ ሌባ ከማለት ምን ልላቸው ኑሮ? ታዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተምሯቸው ዕውቀቱ ሳያንሳቸው ብዙ እየጠበቅንባቸው የአዲሱን ትውልድ ስነ-ልቡና በተሸናፊነት የሚያሽመደምዱና በጉልበት የተቸነከረ ታሪክና ካርታ ሊያወርሱት የሚዳዳቸውን ለምን እንደዚህ አደረጋችሁ ብሎ መጠየቅ ስድብ ሳይሆን በፖለቲካው እሰጥ አገባ ተጠያቂነትን መገንባት ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ጥቃቅን ነገሮች መመልከት ያቃታቸው ምሁራንስ ወደ ይት እየመሩን ነው ብሎ መጠየቅ እውን ስድብ ሊሆን?

ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ታሥራ እንድትፈታ መስዋዕት ለከፈለ ሕዝብ ፣ ከተፈታች በኋላ ዕድሉን አግኝታ በዓለም መድረክ ብቅ ባለችበት ወቅት በአሜሪካ ኮንግሬስ ፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ እስረኞች 100 ናቸው ብላ ባህሰት ስትመሰክር በብዙ ሺሆች የሚቆጠሩ ወገኖች በየጉሮኖው በሚማቀቁባት ፣ ደብዛቸው በሚጠፋባት ሀገር ፤ 80 ሚሊዮኖች ናቸው እንዳትልስ (ፍትሕ በሌለበት ሀገር ሁሉም ዜጋ እሥረኛ ነውና) ፤ ዋሽታለች ብሎ ማጋለጥ ስድብ ነው ተብሎ ሰው ይከሰሳል? ተሳዳቢው ማን ሆኖ?? ከህፃንነታችን ጀምሮ በሕብረ-ተሰባችን ውስጥ የተገነባልንን ሰው የማክበር ሥነ-ልቡናዊ ባሕሪይ ፤ ልምጥምጥ ፖለቲከኞች አዙረው እኛኑ ተሳዳቢ እያሉ ተፈጥሮ የሰጠንን የመናገር መብት ገና የመለስ ዙፋን ላይ ሳይወጡ አፋችንን እየሸበቡት እንደሆነ ልንገነዘብ ያስፈልጋል።

ለማጠቀለል፦

በሀገራችን ላይ የወያኔ ዘረኞች ምንግሥትና እበላ ባይ አጫፋሪዎቹ ፤ ሀገራችን እንደ ሀገር መቀጠል ወደማትችልበት አቅጣጫ በየጀምበሩ እየገፏት እያየን ፤ ጥላቻ የሞላበት የዘር ፖለቲካ የሕዝቡን ቅራኔና ውጥረት እያባባሰው ሄዶ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሌሎች አፍሪካ ሀገሮች የምናየው ዓይነት በዘር ወይም በኃይማኖት ጎራ ተለይቶ ሕዝባችን ሊጨራረስ የሚችልበት ሁኔታ በታሪካችን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ እየተመቻቸ ነው። ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ አለፍ አለፍ ብሎ ቡግ ዕልም የሚለው የእርስ በእርስ መተላለቅ ፤ አሳስቦን ሁላችንም በመታባበር ኢትዮጵያችን በመካባበር ላይ የተመሠረተች አንድነት የሚረጋገጥባት ምድር እንድትሆን ፤ ለፍትህና ለዴሞክራሲ በአንድ ልብ ልንረባረብ መነሳሳታችን የግድ ነው። ችግራችን ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ የሆነ ትውልድ ጠፍቶ ሳይሆን በእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ የሚያወናብዱን ፤ የኛ ብለናቸው የሚገለባበጡብን የሕዝብ ንቀት የተላበሱ የውሸት መሪ ነን ባዮች መድረኩን ማጣበብ ነው። በነሱ ብሶ አንዳንድ ወገኖች ለሚሰነዝሩባቸው ትችት ያገር ያለህ! ተሰደብን! ሲሉን ፈርተን ተስፋ ቆርጠን ዛሬን በዝምታ የምናሳልፍ ከሆነ ለሀገራችን ውድቀት ፣ ለወገኖቻችን ሰቆቃ እያንዳንዳችን ተጠያቂዎች መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። ስለሆነም አድር ባይ ፖለቲከኞች የትግላችንን አቅጣጫ ሲያስቱት ፤ የውሸት ታሪክ ሲያስተምሩ ዝም ብለን ፈርተን ፤ አገር ወዳዶችንና እውነተኛ መሪዎች ተሰሚነት እንዳይኖራቸው አንገታቸውን ሲያስደፉብን ቁመን መመልከቱ ይብቃ! እምቢኝ ማለትና አካፋውን አካፋ ፤ ዘረኞችን ዘረኞች ፤ ባንዶችን ባንዶች በታኞችን በታኞች ማለት መቻል አለብን።

እምቢኝ ለዘረኞች! ለበታኞችና ለባንዶች!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር ያቸንፋል!

አቶሰውየው ከሰሜን አሜሪካ
መገቢት 21 ቀን 2000 ዓ/ም